★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 43 ቁ. 3 ጥር/የካቲት 2010

# *የካቲትን ስናስታውስ*

ወርሃ የካቲት ከዛሬ 102 ዓመት በፊት አባቶቻችን በጣሊያን ቅኝ ገዥና ወራሪ ኃይል ላይ የተቀዳጁትንና የጥቁር ሕዝብ የጀግንነት ተምሳሌት የሆነውን የአድዋን ድል በከፍተኛ ኩራትና ወኔ የምናከብርበት እንዲሁም የካቲት 23 በግራዚያኒ የተጨፈጨፉ ሰማዕታት ወገኖቻችንን በሀዘን የምናስታውስበት ወር ቢሆንም የዛሬ አርባ አራት ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ድምቀትና ታላቅነት የተቀዳጀውን የ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት በአድናቆት የምንዘክርበትም ወር ነው። ይህን አብዮት ምን አመጣው? እንዴት ተከሰተ? ማን ማን ተሳተፈበት? ማንስ ላይ አነጣጠረ? በአብዮቱ ሕዝቡ የአነሳቸው ጥያቄዎች ምን ነበሩ? እንዴትስ ተስተናገዱ? በሂደቱ ምን ምን ተከሰተ? እንቅስቃሴውስ ወደፊት ገፋ ወይስ ተደናቀፈ? ...ወዘተ የሚሉት ጉዳዮች በዝርዝርና በስፋት በየጊዜው የተዘገቡ መሆናቸው ይታወቃል።

በየካቲቱ አብዮት አርባ አራተኛው አመት ላይ ሆነን ዛሬ አገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ ከያኔው ጋር በማነጻጸር ሁኔታዎችን ስንገመግም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይበልጥ አጣዳፊና ወቅታዊ የሆኑ፥ እጅግ በፍጥነት እየተጓዙ ያሉ ጉዳዮች በመኖራቸው፥ ከላይ የደረደርናቸው ጥያቄዎችን አጠቃላይ በሆነ ደረጃም ቢሆን በስፋትና በዝርዝር መመልከቱ ለአሁኑ ወቅታዊ ሁኔታ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል እንላለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘመናትን ባስቆጠረ የጉልተኛ ሥርዓት ሰለባ ሆኖ እድሜ ልኩን ሲማስን ኖሯል። በተለይም በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከአርባ አመት በላይ በንጉሣዊ አገዛዝ ሥር የወደቀው ሕዝብ መረን የለቀቀ ጭቆናና በደል ሳያሰልስ ዘወትር ሲፈፀምበት ቆይቷል። ባመቸበት ሲቃወምና ሲያምፅ፥ ባልቻለበት ምሬቱን ለፈጣሪው እያቀረበ ሳይታክት እሮሮውን ሲያሰማ እንዲሁም ለገዥዎች ጥያቄና አቤቱታ ሲያቀርብ የኖረ ቢሆንም፥ በምላሽ ያገኘው የሚያዳምጠው ቅን ጆሮ ሳይሆን ይበልጥ እመቃና፤ በደል፥ ጭቆና ሆኖ በመቀጠሉ፥ ብሶቱ ሞልቶ መፈንዳቱ አይቀሬ ነበርና ገዢውም ሆነ ተገዢው ሕዝብ ባልጠበቁት ጊዜና ሁኔታ የካቲት ወር ላይ በዚያች ምድር ታስቦም ታይቶም ያልነበረ

የሕዝብ ቁጣ እንደ ደራሽ ውሃ በአራቱም ማዕዘን በአንድ ላይ እየተጠራራ በመሰለ መልኩ ቱግ አለ። ቁጣውንና ምሬቱን ለወዳጅም ለጠላትም በአደባባይ ላይ ዘረገፈው። ፍላጎቱንና ዓላማውን ለጉልተኛው ሥርዓትና ለዚሁ ሥርዓት ተጠቃሚዎችና ደጋፊዎች ለሆኑት፥ እንዲሁም ለዓለም ሕዝብ ጭምር ይፋ አደረገ።

ይህ ሁኔታ በተከሰተበት ወቅት ሥርዓቱ ሊደብቀው የሞከረው ረሃብና ድርቅ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝባችንን እያረገፈ የነበረ ሲሆን ፥ በነዳጅ ዋጋ መናር ክፉኛ የተጎዱ የታክሲ አሽከርካሪዎችን የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። የተጀመረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መመለስ በሚገባቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች ማለትም፥ አርሶ አደሩን ከሰውነት ውጪ አድርጎ ኑሮውን እንዲገፋ ያደረገው የመሬት ሥሪት ይዞታ እንዲያበቃና መሬት ለአራሹ እንዲሆን፥ ዳቦ ለተራበ፥ የሃይማኖት እኩልነት እንዲከበር፥ የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ኢትዮጵያውያን ሴቶች ላይ የሚደርሰው ድርብ ጭቆና እንዲያከትም፥ በላብ አደሮች ላይ አሰሪዎች የሚያደርሱት መረን የለቀቀ ብዝበዛና የመብት ጥሰት እንዲያቆም፥ የሕግ የበላይነት ተረጋግጦ ፍትህ ርትዕ እንዲሰፈን፤ ...ወዘተ በሚሉ አታጋይ መፈክሮች ታጅቦ ወደፊት ገሰገሰ። በገዢውና በተገዢው መካከል የሚኖረው ቅራኔ የማይታረቅ በመሆኑ ጊዜው ሲደርስ የነበረው ግንኙነት ፈርሶ በሌላና አዲስ ግንኙነት መተካቱ አይቀሬ ነበርና የጉልተኛው ሥርዓት እንደቀድሞው ሊገዛ ያልቻለበት ተገዢው ክፍል ደግሞ አልገዛም ያለበት ወቅት ላይ በመድረሱ፤ አሮጌው ሥርዓት እራሱን በሥልጣን ለማቆየት ተከታታይ የጥገና ለውጥ በማድረግ ማዕበሉን ለማቀዝቀዝ ቢሞክርም ሳይሳካለት ቀርቶ ዳግም እንደማይመለስ ሆኖ ለመገርሰስ በቅቷል። ይህ የሕዝባዊው ትግል የመጀመሪያውና ዋናው ድል ሆኖ በታሪክ ተመዘገቦ አልፏል።

በጉልታዊው ሥርወ መንግሥት ወቅት ባህላዊና ማኅበራዊ ከሆኑት ማለትም እድርና እቁብ እንዲሁም ሃይማኖትን ተንተርሰው ከሚፈጠሩት የጽዋ ማኅበሮች በስተቀር ሌሎች መብትን ለማስከበርም ሆነ ጭቆናንና ብዝበዛን ለመታገል የሚረዱ ድርጅትን መፍጠር ሆነ ተቋማትን ማዋቀር አጥብቆ የተከለከለ ነበር። ይሁንና በዚሁ ከባድና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም በትግል ሊቋቋሙ የቻሉት የሠራተኞችና የሙያ ማህበራት እንኳ ከተፅእኖ ነፃ የሆኑ አልነበሩም። በወቅቱ በፖለቲካ መደራጀት ይቅርና ፖለቲካ የሚለውም ፅንሰ ሃሳብ ራሱ በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ጨርሶ የሚታሰብም የሚታወቅም አልነበረም። ሳይታሰብ በግብታዊነት በተጀመረው የሥር ነቀል ለውጥ እንቅስቃሴ የተነሱት ሕዝባዊ ጥያቄዎች በሂደት መልስ እንዲያገኙና ሕዝባዊ ትግሉ የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ከዳር ለማድረስ ይቻለው ዘንድ በቅጡ አስፈላጊ የሆነውን የትግል መሣሪያ፥ ማለትም ትግሉን የሚያቀነባብርና አቅጣጫ እየሰጠ የሚያደራጅና የሚመራ

ድርጅት እንዲኖረው ሁኔታው ሳይፈቅድለት ቀርቷል። ግና ቀደም ብለው ሥርዓቱ እያደረሰ ያለውን በደልና ጭቆና ሲያጋልጡና ሲቃወሙ የነበሩት፣ የመማር እድሉን ያገኙ፣ በውስጥም በውጭም የሚገኙ ተማሪዎች፣ ራሳቸውን ቀደም ብለው በተማሪ ማኅበራት አደራጅተው ሲታገሉ የነበሩ ሲሆን በኋላም ከተማሪ ማኅበር ላቅ ያለና የመሪ ድርጅት ሚናን ሊጫወቱ የሚችሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመመሥረት ችለዋል። ኢሕአፓ አብዮቱ ከመፈንዳቱ ከሁለት አመት በፊት ማለትም በሚያዚያ ወር 1964 ዓም የተመሠረተ ሲሆን አብዮቱ ከተከሰተ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ራሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነሐሴ 26 1967 ዓም ላይ ይፋ አደረገ። የኢሕአፓ መመሥረት ትግሉ በዋናነት ይጎድለው የነበረውን ክፍተት በማሟላት አንድ አማራጭ የትግል መሣሪያ፣ መሪ ድርጅት እንዲኖረው አስቻለ። በማናቸውም መስክ ሕዝቧን በዕኩልነት የምታስተናግድና ሕግ የበላይ የሆነባት ሀገር ዕውን እንድትሆን መታገል የዓላማዬ አልፋና ኦሜጋ ነው ያለው ኢሕአፓ፣ በየካቲቱ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ራሱን ይፋ ለማድረግ መብቃቱ እንቅስቃሴው ካስመዘገባቸው ድሎች አንዱ ሆኖ በታሪክ እንደሚጠቀስ እሙን ነው።

ከየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ቀደም ብለው በተማሪዎችና በሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች በሥርዓቱ ላይ ያነጣጠሩ ግን ደግሞ በተናጠል ይደረጉ የነበሩ ትግሎች ያበረከቱት ድርሻም ለእንቅስቃሴው መንገድ የጠረገ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። እንዲያውም ሕዝባዊ አመፁን ሁሉም እንዲሳተፍበትና ወርድና ስፋቱም በሂደት እየጨመረ ሁሉንም ያካተተ ለመሆን በመብቃቱ ትልቅነቱንና ደማቅነቱን ያረጋገጠ እንደነበር ከቶ ዋቢ የሚያስጠራ አልነበረም፣ አይደለምም።

በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አብዛኛው ሕዝብ ከግፋና ከጭቆናው በተጨማሪ በጉልተኛው አገዛዝ ታፍኖና ተቀፍድዶ እንዲኖር የተገደደ ስለነበር ከራሱ ውጭ ዘልቆ የውጭውን የዓለም ሁኔታ የሚሰማበትም ሆነ የሚያይበት እድሉ እጅጉን የመነመነ ነበር። ይህም በመሆኑ ምንም እንኳን በግብታዊነት የጀመረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሥርዓቱን ለመደምሰስ ቢበቃም፣ በወቅቱ ግን የተገኘውን ድል ጠብቆ ሌሎችንም ጥያቄዎች በየደረጃው መልሳቸውን እንዲያገኙ ለማድረግና የትግሉም ግብ ዳር እንዲደርስ ለማስቻል ሕዝቡ ወሳኝ የሆነውን መሪ ድርጅት አለማግኘቱ ችንፈቱ ነበር ለማለት ባያስደፍርም ጉዳቱ ነበር ማለቱ ግን የሚያስኬድ ነው ብለን እናስባለን። ከተመሠረተ በሶስተኛ አመቱ ውስጥ ራሱን ለመላው የአትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ይፋ ያደረገው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ - ኢሕአፓ - ትግሉን የመምራት ኃላፊነቱን ወስዶ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሕዝብን አመኔታና ተቀባይነት ለማግኘት የቻለ፤ ለአገራቸውና ለወገናቸው ሲሉ ሊከፈል የሚገባውን መስዋዕትነት ሁሉ በፀጋ ለመክፈል የተዘጋጁ መሪዎችና አባላት ያሉት መሪ ድርጅት መሆኑን ያስመሰከረ መሆኑ የተጠበቀ ቢሆንም፣ በጊዜው ግን የተፈጠረውን

የሥልጣን ክፍተት ለመሙላት ጥንካሬ አልነበረውም። በመሆኑም በወቅቱ ሥልጣን ፣ ከወታደራዊ ክፍሎች ተውጣጥተው፤ የወል ስማቸውን ደርግ ብለው በሰየሙ የምርጥ መኮንኖች ቡድን ሊገባ ችሏል። በዚህ ጊዜ ላይ ነበር የየካቲት 66-ቱ ሕዝባዊ አመፅ ያነሳቸው ጥያቄዎች፥ የሰነቀው ብሩህ ተስፋና በትግሌ እውን አደርጋታለሁ ያላት የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ጉዞ የዋዛ እንደማይሆን በማስጠንቀቅ የመጀመሪያው ደወል በአራቱም ማዕዘን ያቃጨለው። እነሆም ይህ የምርጥ መኮንኖች ቡድን በሂደት በራሱም ውስጥ ለትግሉ ቀና አመለካከት ያላቸውን ሁሉ ፈጅቶ፤ የቀድሞ ባለሥልጣናትንም በአንድ ሌሊት አርዶ፤ በሕዝቡ የቀረበውን "ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት" መመሥረት ጥያቄን አሻፈረኝ በማለት በጊዚያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ተካው። የባንዳ ምሁራንንም ድጋፍ አገኘ። ኢሰፓ በሚባል ፓርቲ ተደራጅቼያለሁ፤ መንግሥቱ ኃ/ማርያምንም የፓርቲው መሪና ሊቀመንበር መሆኑንም አውጀያለሁ ብሎ ተፈፀመ። ከዚያ በኋላ በአገሪቱ ለተነሱ ጥያቄዎችና ችግሮች ሁሉ መልሳቸው የፋሽስታዊው ወታደራዊ መንግሥት ግድያና ጦርነት ብቻ ሆነ። ኢትዮጵያ እስከ ወዲያኛው ምትክ የማይገኝላቸውን ብሩህና እምቅ እውቀት ያካበቱ ልጆቿን፣ ፋሽስቶች፥ "ቀይ ሽብር" በሚሉት ፅልመት ፈጁ። አገሪቱ ያፈራቻቸው የመከላከያ ሠራዊቱን የመምራት እውቀትና ልምዱን ያካበቱ አገራቸውንም የሚወዱ የጦር መሪዎቿን አንድ አልባሌ ኮሎኔል በሚያዟቸው ወታደሮች ፊት ማዕረጋቸውን እየገፈፈና እያዋረደ ከፍተኛ የስነ ልቦና ሰለባ እንዲደርስባቸው አደረገ። ለሥልጣኔም ተቀናቃኝ ናቸው የሚላቸውን አንድ ባንድ ለቅሞ ፈጀ። ኢትዮጵያን እንዳለ ለአስራ ሰባት ዓመታት ጽልመት አልብሶ ጊዜው ሲደርስ መሪው አገር ለቆ ከመፈርጠጡ ሌላ ኢሰፓ የተባለውም ጭምብል እንዲያከትምለት ሆነ። ይህ ኢትዮጵያን የገደለና ለውጭም ሆነ ለውስጥ ጠላቶቿ ያጋለጠ ኃይል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ክፉ ጠባሳን አስመዝግቦ አልፏል። የካቲት በየዓመቱ በመጣ ቁጥርም የየካቲት 12 ሰማዕታትን ስንዘክር፥ አንፀባራቂውን የአድዋ ድል ስናከብር፥ ለአስራ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያን መቀመቅ ውስጥ የከተታትን ፋሽስታዊ ፅልመትም ማማተራችን አይቀሬ እንደሚሆን መጥቀሳችን ተገቢ ነው ብለን እናስባለን።

በ1983 ዓም በውጭ ኃይሎች ድጋፍ አማካኝነት በሕዝባችን ጫንቃ ላይ በኃይል የተቀመጠውን ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ማንነትና ላለፉት 27 ዓመታት በአገሪቱ በመላ ያደረሰውን ዘርፈ ብዙ የግፍና የበደል ስንክሳር መዘርዘር የሚያስፈልግ ሆኖ አላገኘነውም። ባለፉት 27 ዓመታት በሀገሪቷ በየትኛውም ማዕዘን ቢሆን በጠባቡ አምባገነን አገዛዝ ያልተነካ ወገን ባለመኖሩ ሕዝቡ በቃኝ ብሎ መነሳቱንና ግብ ግብ መግጠሙን እያየን ስለሆነ የነገር ቋንጣን ቢያበዙት በአህያ አይጫንም ነውና ወደ ዝርዝር ሳንገባ ማለፉን መርጠናል።

ዛሬ በአገራችን ውስጥ የወያኔ ያላሰለሰ ጥቃት፥ጭቆናና በደል፥ አልፎ ተርፎም እብሪትና ንቀት ከአፍ እስከ ገደፉ በመሙላቱ ከእንግዲህ ይህን መሸከም አይቻለንም ያለው ዜጋ እምቢተኛነት በመላ የአገሪቱ ክፍሎች እያስደመመ ይገኛል። ቢመከር ቢዘከር አልሰማን ያለውን፥ ትዕግሥትን እንደሞኝነት፥ ነገር ማስጨረስን እንደፍርሀት ወስዶ የሕዝብን ኃያልነትና ታላቅነት ንቆ በማን አለብኝነት ተወጥሮ የከፋ የከረፋውን እኩይና አረመኒያዊ ተግባሩን በመቀጠል ላይ የሚገኘውን ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነውን የወያኔ አገዛዝ ከእንግዲህ ላንዴም ለሁልጊዜውም በማያዳግም ሁኔታ ድባቅ መቶ ከኢትዮጵያ ምድር ላይ ጠራርጎ ለማስወገድ ሥንቁን ሰንቆ ተነስቷል። የወያኔን አገዛዝ ስንል የወያኔው ድርጅት የአገዛዝ ሥርዓት ማለታችን እንጅ በምንም ዓይነት መንገድ የትግራይ ሕዝብ ማለታችን እንዳልሆነ ሊሰምርበት ይገባል። የትግራይ ሕዝብና ወያኔ አንድ ናቸው በማለት የማይሆን ጭምብል አጥልቆ የሚያቅራራው ወያኔ ብቻ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክ ቁልጭ አድርጎ እንደሚያሳየው ሕዝቡ እጅጉን አርቆ አስተዋይ፥ ታጋሽ፥ በመንፈሳዊ ዕምነቱ የፀና ፍቅርን እንጂ ጥላቻን የማያቀነቅን፥ አብሮነትን እንጂ መነጣጠልን የማይሻ፥ ታታሪ፥ ጠንካራ ሠራተኛ፥ ተመራማሪና አፍላቂ፥ የሰውን የማይፈልግ የራሱን የማያስነካ፥ አስቀድሞ የማይተናኮል ከነኩት ግን አምቢኝ የሚል፥ አብሮ መብላት መጠጣትን፣ መካፈልን ዋና ባህሉ ያደረገ፥ ለነፃነቱ ቀናዒና አገሩን እጅግ አድርጎ የሚወድ፥ ከሌሎች አገር ሕዝቦች ጋር በመልካም ጉርብትና መኖርን የሚፈልግ እንግዳ ተቀባይ ሕዝብ ነው። እኒህ ባህሪያቱ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ የሕዝባችንን ማንነት የሚገልፁ ትሩፋቶቹ ናቸው። እነዚህን አኩሪ ቅርሶቹን ለማውደም የዛሬ ሃያ ሰባት ዓመት፣ በሁኔታዎች፣ በውጪና በአገር በቀል ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይላት ድጋፍ በሕዝባችን ጫንቃ ላይ እንዲሰፍር የተደረገው ዘረኛውና ከፋፋዩ የወያኔ አገዛዝ እጅጉን ብዙ ደክሟል፤ ብዙ ብሏል፤ ብዙ ቀጥፏል ብዙ ጥሯል፤ ዛሬም ድረስ ሳይታክት ይህንኑ እኩይ ተግባሩን ቀጥሎበታል። ሆኖም ግን የዚህ ሁሉ ድካሙ ውጤት ሌላ ማንንም ሳይሆን ይህንኑ እብሪተኛ ከፉኛ አስደንግጦታል፥ የሚይዝ የሚጨብጠውን አሳጥቶታል። እንቅልፍም በአያሌው ነስቶታል። እናም ጊዜው ሲደርስ በዛሬውም ወጣት ትውልድ ውስጥ እነዚሁ የሕዝባችን እሴቶች ታምቀው ቆይተው ኖሮ፤ በወለጋ በአርሲ፥ በሐረርጌ በባሌ፣ በሸዋ በጎንደር፣ በጎጃም በወሎ፣ በጅማ በሲዳሞ፣ በኢሉባቡር በጋምቤላ፣ ...ወዘተ ፍንትው ብለው ታይተዋል።

ስለሆነም ይህ የተጀመረው የሕዝብ እምቢተኛነት ትግል በድል አድራጊነት ይጠናቀቅ ዘንድ፤ **በውስጥም በውጭም የሚንገኘው ሴቱም ወንዱም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዋናውና ዐቢይ የሆነውን፣ ኢትዮጵያን የመታደጉን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት ታላቅና ክቡር የሆነውን የህይወት መስዋዕትነት ከመክፈል ጀምሮ ትግሉን ሊረዳ የሚችል ማናቸውንም ነገር ለመቀበልና ለማድረግ በቁርጠኛነት ዝግጁነታችንን**

***የምናረጋግጥበት ወቅት ላይ ደርሰናል። ከእንግዲህ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ እንደማንል ቃል ገብተናል። ተማምለናል። ሂደቱ አልጋ በአልጋ እንደማይሆን አስቀድመን ተረድተናል፤ መውጣት መውረድ፥ መውደቅ መነሳት፥ ወደፊት መገስገሥ ወደኋላ ማፈግፈግ ሊኖር እንደሚችልም ከልምዳችን ገብይተናል፤ በዚህ ትንቅንቅ ሂደት ውስጥ መሞት፥ መራብ መጠማትም እንደዚሁ አይቀሬ እንደሆኑ ነጋሪ አያሻንም። ውስጡ ኖረን በውስጡ አልፈን ዛሬም ድረስ ይህንን ዘረኛ ኃይል ጠፍንገን ይዘን ሁላችንም ታግለነዋል። ያም በመሆኑ፥ በታሪካችን ስንክሳር ውስጥ ኢትዮጵያን ያጋጠማት እጅግ ክፉ ዘመን ከሚባሉት ብለን ልንዘግበው የምንችልበትን ጊዜ ለማሳጠር ሁሉም የሚተጋበት ወቅት አሁን ነው። እናም ክብርና ነፃነትን ለመጎናፀፍ ምን ያህል እንደሚጠይቅ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እንግዳ ነገር አይደለም። ደግመን ደጋግመን የሠራነው ታሪካችን ነውና ዛሬም በተባበረ ትግላችን ይህንኑ የምንታወቅበትን ባህል ደግመን እንደምናድሰው በኛ በኩል አንዳችም ጥርጣሬ የለንም። ይብላኝ ለዘረኛው <u>ወያኔና ለደጋፊዎቹ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሁሉ</u>!***

*የሃገራችንን ህልውና ማስከበሩን በዋናነት ለሚወስዱ ኢትዮጵያዉያን ሁሉ፤ ዛሬ ይህንን ተቀዳሚ አጀንዳ አርጎ ከመንቀሳቀስ አኳያ ሌሎችም በአገሪቱ ውስጥ ወደ ኋላ ሊሏቸው የማይቻላቸው እውነታዎች፣ መለስተኛና ሊታረቁ የሚችሉ ጉዳዮች እንዳሉ በቅጡ በግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ ተገቢ ይሆናል። በትግሉ ሂደት ውስጥ ልንፈታቸው የምንችላቸውን እልባት እንዲያገኙ እያደረግን፤ በመካከላችን እምነትንና መተሳሰብን እያጎለበትን፤ በሂደቱ መፍታት ያልቻልናቸውን ከወያኔ ውድቀት በኋላ በምንመሠርታት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ መልሳቸውን ያገኙ ዘንድ የሚያስችል መድረክ እውን እንዲሆን ሁሉም በቅንነትና በጋራ ለመፈታታቸው ከወዲሁ ራሱን ዝግጁ አድርጎ መገኘት ይጠበቅበታል ብለን እናስባለን።*

*እንደሚታወቀው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ካስገመገመበት ጊዜ አንስቶ፥ በትግሉ በሚያስወግደው ሥርዓት እና በሚተካው አዲስ ሥርዓት መካከል ድልድይ ሆኖ የሚያገለግለው፤ በሰከነና ሁሉን ባሳተፈ ደሞክራሲያዊ መንገድ፣ ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር ወቅት ለማዘጋጀት ሲችል ነው። ከዚህ በፊት በነበሩት አጋጣሚዎች ማለትም የጉልተኛው ሆነ የደርግ አምባገነን ሥርዓቶቶች ሲደመሰሱ ለሕዝቡ መብት ሊያጎናጽፍ የሚችል ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሁኔታ ባለመፈጠሩ አምባገነኖች የሕዝቡን ትግል ለመሞጭለፍ ችለዋል። በመሆኑም ላለፉት አርባ አራት አመታት አገራችን የአምባገነኖች ሰለባ ሆና እዚህ ደርሰናል። ከወያኔ አምባገነን ሥርዓተ ህልፈት በኋላ ለምትፈጠረው አዲሲቷ ኢትዮጵያ ወሳኝ የሆነውን ሁሉን አቀፍ የሽግግር ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሶስተኛ ጊዜ እንዳያጣው፣ አገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ*

ሁሉ ለተግባራዊነቱ አጥብቆ እንዲታገል ሀገራዊ ኃላፊነትና ግዴታ ይኖርበታል። ይህ እውን እንዲሆን ኢሕአፓ የበኩሉን ለማድረግ ሁሌም ዝግጁ ነው።

ሕዝባዊውን እምቢተኛነት የማቀጣጠሉንና ይበልጥ የማጎልበቱን ሥራ ለሰኮንድም ቢሆን ሳናዛንፍ የሚከተሉትንም በሥራ ላይ ለማዋል እንትጋ።

- የኃይል ሚዛኑ እንዲለወጥ ለማድረግ የሕዝባዊ እምቢተኛነቱን እንቅስቃሴ በሁሉም ቦታዎች ማስተባበር፥ ማቀናጀት፥ ብሎም በቀጣይነት ማስኬድ፤
- ወያኔ ውስጥ ትርምስ ሊፈጥሩ የሚችሉ ክንዋኔዎችን በሙሉ በስልትና በዘዴ ማከናወን፤
- ወያኔ ይበልጥ በሕዝብ እንዲተፋና እንዲገለል የሚያስችሉ ሥራዎችን ማስፋፋት ማጠናከር፤ በቀጣይነት ለተግባራዊነታቸው በፅናት መንቀሳቀስ፤
- ይህን አገር የማዳን ትግል ለማቀዝቀዝ፥ ለማብረድ፣ ለማደናቀፍ ብሎም ለማስቆም የሚደረጉ ከየትኛውም አቅጣጫ ሊመጡ የሚችሉትን ማናቸውንም ዓይነት እንቅስቃሴዎች ነቅቶ በመከታተል በተቀነባበረና በተቀናጀ መልክ መታገልና ማምከን፤
- ከወያኔ ጋር መወያየት መደራደር እርቅ የሚሏቸውን ያረጁ ያፈጁ ቀልዶች ከቁጥር ውስጥ አለማስገባት ወቅታዊነት አላቸው።

እነዚህንና ሌሎችንም አዘናጊ ድርጊቶች አምረን መታገላችን ለነገ የሚባሉ ስላልሆኑ ሁሉም በያለበት ለሕዝባዊው እምቢተኛነት ትግል ዘብ እንዲቆም ኢትዮጵያ ከምንጊዜውም በላይ አጥብቃ እየጠየቀችን ነውና ጥሪያዋን ሰምተን እንታደጋት።

በተባበረ ትግላችን ወያኔን ማስወገዳችን አይቀሬ ነው!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል!!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!!